# መጽሐፈ ዕዝራ (59)

## ጥናት አንድ ዕዝራ 1፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር የፍጥረት ሁሉ ገዥ ስለሆነ፤ አንዳንድ ጊዜ እኛ በጭራሽ ልንገምተው ከምንችለው መንገድ ውጭ ደህንነታችንን ሊያመጣልን የሚችል አምላክ እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ፣ ስለመረጥኩት ስለ እስራኤል፣ አንተ ባታውቀኝ እንኳ በስምህ ጠርቼሃለሁ፣ የክብርም ሥም ሰጥቼሃለሁ።” ኢሳ 45፡4

1. መጽሐፈ ዕዝራ 1፡1-11 በአንድነት ይነበብ። ቁ1ድን ስናነበ፤ ነገሥታቶች እንደነገሱ በመጀመሪያ ለማከናወን የሚፈልጉት አጀንዳ በውስጣቸው ምናልባትም ለረጅም ጊዜያት በልባቸው የተቀመጠና አንገብጋቢ ሆኖ የሚያዩት ነገር እንደሚሆን ይታወቃል፤ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ገና ንግሥናውን በጀመረ በመጀመሪያው ዓመት ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ይህንን የምዕራፍ መጀመሪያ የሆነውን ቁ1 ብቻ በማንበብ እግዚአብሄር ይህንን ታላቅ ንጉስ እርሱ ራሱ የሚያስበውን ሳይሆን እግዚአብሄር የሚፈልገውን ጉዳይ እንዲያደርግ ስላደረገበት መንገድ ክፍሉ ምን ይነግረናል?
2. ንጉሱ ቂሮስ በዚሁ በቁ1 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር መንፈሱን አነሳስቶ ውሳኔውን ለማስተላለፍ በወሰነበት ወቅት ውሳኔውን ያስተላለፈባቸው ሁለቱ መንገዶች ምንና ምንድናቸው? ይህንን ያህል ታላቅ ንጉሥ ሕዝቡ እንዲታዘዘው ለማድረግ በቃል ብቻ አዋጅ ቢያስነግር በቂ ሊሆን ይችላል፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል በአዋጅ ከማስነገር አልፎ በጽሑፍም እንዲቀመጥ የወሰነው?
3. በቁ2 ላይ ስንመለከት ይህ የአህዛብ ንጉስ የሆነው ንጉሥ ቂሮስ ከእግዚአብሄር እንደሆኑ አምኖ የተቀበላቸውና ለሰዎችም ምንጫቸው ከየት እንደሆነ ለመግለጽ ያላፈረባቸው፤ቢያንስ ሁለት ነገሮች እንደነበሩ ማየት እንችላለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። ንጉሱ በቁ2 ላይ ከተናገራቸው ነገሮች መሃል “…በኢየሩሳሌምም ለእርሱ ቤተ መቅደስ እንድሰራ አዞኛል።” የሚል ነው፤ ቂሮስ ይህንን ማለቱ እውነትም እግዚአብሄር የቤተ መቅደሱን ሥራ ሃላፊነት የሰጠው ለዚህ ንጉሥ ነው ማለት ነው ወይስ አባባሉን የምትረዳው በምን መንገድ ነው?
4. ቁ3ንና ቁ4ትን ስናነብ ንጉሱ ቂሮስ በመንግሥቱ ውስጥ የሚኖሩትን አይሁዶች በሁለት ዓይነት በመክፈል ነው ሲያናግራቸው የምንመለከተው፤ ይህ ንጉሥ አይሁዶቹን የከፈለባቸው መንገዶች ምንና ምን እንደሆኑ ከእነዚህ ሁለት ቁጥሮች በመነሳት ተናገር። እነዚህ ሁለቱ ዓይነት ሰዎች ቤተ መቅደሱን ከመስራት አኳያ በንጉስ ቂሮስ ዓዋጅ መሰረት የሚጠበቅባቸው ምን እንደሆነ ተናገር። አንተስ የእግዚአብሄርን ሥራ አስመልክቶ በሥራው ላይ ተሰማርተህ ከጠላት ጋራ ትፋለማለህ ወይስ በሩቅ ሆነህ ገንዘብህን መስጠት ብቻ በቂ ሆኖ ይታይሃል? ያንንም ለማድረግ በሰው ተገፍተህ!
5. ንጉሱ ቂሮስ በአዋጁ ውስጥ እንደተናገረው በኢየሩሳሌም ሊሰራ ያለውን የእግዚአብሄርን ቤት ለመስራት ለሜሄድ ያልተነሱ ሰዎችም እንደነበሩ እንረዳለን፤ ለምን ይመስልሃል ከፊሎቹ ለመሄድ ሲነሱ ከፊሎቹ ደግሞ ለመሄድና ለመስራት ያልተነሱት? በቁ1 ላይ ስለ ንጉሥ ቂሮስ በተነገረው ነገርና በቁ5 ላይ ደግሞ ስለ ይሁዳና የብንያም ቤተሰብ አለቆች፣ እንዲሁም ካህናትና ሌዋውያኑ ሲነገር በምናየው ሃሳብ መሃል የሚታይ አንድ ትልቅ የሚያመሳስላቸው ነገር አለ፤ ይህ አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ?
6. በቁ2-4 ላይ ንጉሱ ቂሮስ በአዋጁ ውስጥ ካካተታቸው ነገሮች መሃል በቁ5-7 ውስጥ ወዲያው ተፈጻሚነት ሲያገኙ የሚታዩት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር።
7. ኢሳ 45፡4-5 ላይ እግዚአብሄር ስለ ቂሮስ ሲናገር ሁለት ጊዜ “አንተ ባታውቀኝም እንኳን” በማለት ይናገራል። ከእግዚአብሄር ጋራ ትውውቅ የሌለውና ማንም ሰው ለአይሁድ ደህንነት በእርሱ በኩል ይመጣል ብሎ በማይገምተው ሰው መጠቀሙ ለእኛ ምን ሊያስተምረን ይችላል? አንተስ እግዚአብሄር በጭራሽ ባላሰብከው ሰውና ባላሰብከው መንገድ ማዳኑን አምጥቶልህ ያውቃል ወይ? እግዚአብሄር እኛ ከምንገምተውና ከመናስበው መንገድ ውጭ ደህንነታችንን ሊያመጣልን አምላክ እንደሆነ መዘንጋት የሉብንም።

<u>ጥናት ሁለት ዕዝራ 3፡1-13</u>

የጥናት ዓላማ፡- ከሌሎች ጋራ የእግዚአብሄርን ሥራ እሰራለሁ የሚል ማንኛውም ክርስትያን፤ በአንድ ልብና በአንድ አላማ በተሰማራበት ሥራ ላይ መሰለፍ አማራጭ የሌለው ነገር እንደሆነ መቀበል እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሰባተኛው ወር በደረሰ ጊዜ፣ እስራኤላውያን በየከተሞቻቸው ሳሉ፣ ሕዝቡ እንደ አንድ ሰው ሆነው በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ።" ዕዝ 3፡1

1. መጽሐፈ ዕዝራ 3፡1-13 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3ትን ብቻ በማንበብ የታሪኩ ተዋናኞች እንደሆኑ የምታያቸውን ሰዎች ሁሉ ማን ማን እንደሚገኝበት በመዘርዘር ተናገር። በቁ1 ላይ "ሕዝቡ እንደ አንድ ሰው ሆነው በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ።" በማለት ይናገራል። ጸሐፊው ይህንን "እንደ አንድ ሰው" የሚለውን አባባል ሲጠቀም ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
2. ጳውሎስ በፊሊ 1፡27 ላይ የፊሊጵሲዩስን አማኞች እንዲያደርጉት የሚጠይቃቸው ነገር፣ በዕዝራ 3፡1 ላይ ሕዝቡ ያሳዩት ነበረው መንፈስ ጋራ ሲተያይ ሁለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊያመሳስላቸው የሚችለው ምን ሃሳብ እንዳለ አስረዳ።
3. በቁ1 ላይ የምንመለከታቸው ሰዎች፣ ማለትም ኢያሱና ካህናት ዘመዶቹ፤ እንዲሁም ዘሩባቤልና የሥራ ባልደረቦቹ ሁሉ የሚሰራው ሥራ በዘፈቀደ ሳይሆን ጥንቃቄ በተሞላበት መልክ መስራታቸውን የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? ምዕራፍ 3ትን በአጠቃላይ ስንመለከት በተለይም ቁ2ትንና ቁ6ትን ስናነብ መሰዊያው ከቤተ መቅደሱ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደተሰራ እናያለን፤ ከዚህ ከአሰራራቸው ቅደም ተከተል ለእኛ ህይወት ትምህርት ሊሆነን ምን ነገር ማግኘት እንችላለን ትላለህ?
4. ቁ3 "በዙሪያቸው ካሉት አህዛብ የተነሳ ፍርሃት ቢያድርባቸውም፣ መሰዊያውን በቀድሞው መሰረት ላይ ሰሩ።" ፍርሃት ብዙ ጊዜ የምንፈልገውን ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ የሚያስቀረን ነገር እንደሆነ ይታወቃል፤ ለምን ይመስልሃል እነዚህ ሰዎች ከፍርሃት የተነሳ መሰዊያውን ከመስራት ወደ ኋላ ከማለት እንቢ ያሉት? መሰዊያው የተሰራው ለታይታና መሰዊያ አለን ለማለት ብቻ እንዳልሆነ ልናውቅ የምንችልበት ምን መንገድ ይታይሃል?
5. ቁ8-9ኝን በማንበብ በኢየሩሳሌ የነበረው የእግዚአብሄር መቅደስ የተጀመረው መቼ እንደነበረ ተናገር። ቁ8-11 ላይ ያለውን ስናነብ ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች በተለያየ መንገድ ተደራጅተው ሥራውን እንደጀመሩ ይነግረናል፤ በዚህ ቦታ ሰዎቹ ተከፋፍለው እያደረጉ የምታያቸውን የሥራ ክፍፍል ዓይነቶች በመዘርዘር ተናገር።
6. በቁ10 እና በቁ11 ላይ ስናነብ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ መጀመር ምክንያት ዝማሬ እንደተዘመረ እንመለከታለን። በዚህን ወቅት የተመረጠው መዝሙር ምን የሚል ነበረ? በዚህ ዝማሬ ላይ ሲሳተፉ የምናያቸው እነማንን ነው?
7. በቁ12 እና በቁ13 ላይ ስትመለከት የቤተ መቅደሱ መሰረት መጣል በሕዝቡ ውስጥ የፈጠራቸው ሁለት ዓይነት ስሜቶች ምንና ምን እንደነበሩ ተናገር። እነዚህን ሁለት ዓይነት ስሜቶች ያሳዩትን ሰዎች በሁለት ጎራ ከፍሎ ነው የሚያሳየን፤ እነዚህ ሁለት ግሩፖች ምንና ምን ተብለው ነው የተከፈሉት?
8. ትንቢተ ሐጌ 2፡3-7 ላይ የምናነበው ሃሳብ በዚህ ክፍል የሚያለቅሱት ሰዎች አጥጋቢ ምክንያት እንዳልነበራቸው የሚጠቁምህ ሃሳብ የትኛው ነው? አንተስ ዛሬ እግዚአብሄር በሚሰራው ነገርና በእግዚአብሄር መገኘት ከመደሰት ይልቅ ባለፈው ትዝታ ብቻ ተይዘህ ራስህን ታስታምማለህ ወይ?
9. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ1ንና ቁ6ትን ስንመለከት፤ እንደ አንድ ሰው ሆኖ የተሰበሰበው ህዝብ ለመስዋዕት የሚሆነውን መሰዊያ አዘጋጅተው የጨረሱት በአንድ ቀን እንደሆነ እናያለን። በሕዝቡ ዘንድ የታየው የልብ አንድነት ለሥራቸው ክንውን ማለትም በአንድ ቀን ውስጥ ሥራውን ለመጨረስ ረድቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? አብረህ ከተጠመድካቸው ወገኖች ጋራ በአንድ ልብ ለማገልገል ተቸግረህ ታውቃለህ ወይ? የእግዚአብሄርን ሥራ በሚገባ ለመሥራት ካስፈለገ ከሌሎች ጋራ እንደ አንድ ሰው በአንድ ልብና በአንድ ዓላማ ሆኖ መሥራት ወሳኝነት እንዳለው መዘንጋት አይገባንም።

# ጥናት ሶስት ዕዝራ 4፡1-24

የጥናት ዓላማ፡- ጠላታችን ሰይጣን አንድ ጊዜ ስናሸንፈው በቃ ተሸንፌአለሁ ብሎ አይተወንም፤ ይህንንም እውነት መማር የምንችለው አይሁድ ካለፉበት ብቻ ሳይሆን ሉቃስ በወንጌሉ እንደሚነግረን፤ ዲያቢሎስ በኢየሱስ መሸነፉን ቢያምንም የተለየው ግን ለጊዜው ብቻ እንደነበረ ሉቃስ ስለሚነግረን፤ እኛም እስከጊዜው እንጂ ለሁልጊዜ ከፈተና አመልጣለሁ ብለን ራሳችንን ማታለል እንደሌለብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ዲያቢሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ ሌላ አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከእርሱ ተለየ።” ሉቃስ 4፡13

1. ዕዝራ 4፡1-24 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ውስጥ ስናነብ አይሁድ የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ ለመስራት ሲነሱ እኛም ከእናንተ ጋራ አብረን መቅደሱን እንስራ ባዮች እንደተነሱ እንመለከታለን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ጸሐፊው እነዚህን አብሮ ለመስራት ጠያቂዎችን ማን በማለት ነው የሚጠራቸው? እነዚህ ቤተ መቅደሱን ከአይሁድ ጋራ በመተባበር ለመስራት የተነሱት ሰዎች እግዚአብሄርን እውነትም በአምላክነቱ እንዳልተቀበሉት ከአነጋገራቸው የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው?
2. በቁ1-6 ላይ የይሁዳ ጠላቶች የቤተ መቅደሱን ሥራ ለማስተጓጎል የተለያዩ ሴራዎችን ለመጠቀም እንደሞከሩ እንመለከታለን። ቤተ መቅደሱን አብረን እንስራ የሚለውን የመጀመሪያውን የጠላት ጥያቄ ስርመለከት ለእግዚአብሄር ሕዝቦች ሊኖረው የሚችለው ችግርና ሊያስከትለው የሚችለው ምን ነገር አለ ብለህ ታምናለህ? አንተስ ለእግዚአብሄር የሚሆነውን ነገር ከማይሆን ነገር ጋራ ቀላቅለህ ለማቅረብ ተፈትነህ ታውቃለህ ወይ?
3. ቁ8-10 ላይ የክሱን ደብዳቤ ጽፈው ለንጉሥ አርጤክስስ ሲልኩ በክሱ ተባባሪ እንደነበሩ ሥማቸው የሰፈረውን ቢያንስ አራቱን ግሩፖች በመዘርዘር ተናገር። ይህንን የስም ዝርዝር ንጉሱ በሚያነብበት ጊዜ የመሰረቱት ክስ ምን ያህል ሰዎችን ያካተተና በንጉሱ ዓይን አሳማኝነት ያለው ነው ለማለት ይቻላል?
4. በቁ12 ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች ስናነብ በአካባቢው የሚኖሩት ሰዎች የክስ ደብዳቤአቸውን ሲጽፉ ለኢየሩሳሌም መጠሪያ አድርገው የተጠቀሙባቸው ስሞች ምን የሚሉ ናቸው? በንጉስ ቂሮስ ትዕዛዝ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ስለተመለሱት አይሁዳውያን እነዚህ የአካባቢው ሰዎች ሲናገሩ የምንሰማው እውነተኛ ምስክርነት ምንድነው?
5. ቁ13-15ትን ትኩረት ሰጥተን ስንመለከተው፤ እነዚህ የአይሁድ ከሳሾች ይህንን ደብዳቤ ለመጻፍ ለተነሳሱበት ነገር ሁለት ነገሮች ምክንያት እንደሆኗቸው ይናገራሉ፤ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። እነዚህ አይሁድን የሚከሱት ሰዎች የንጉሱንም ሆነ ከእርሱ ጋራ የሚሰሩትን ባለሥልጣኖች ትኩረት እንደሚስብ አውቀው በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የመረጡት አንድና ዋነኛው ነገር ምንድነው? አንተስ ራስህን ስርመለከተው ከገንዘብ ጋራ ያለህ ትስስር ምን ይመስላል?
6. ቁ15 “እንግዲህ ከተማይቱ የተደመሰሰችው በዚህ ምክንያት ነው።” በማለት በክሱ ላይ ያሰፈሩት ሃሳብ ምናልባትም እነዚህ ሰዎች ለመዋሸትና ነገራቸው እንዲሰማላቸው ያቀረቡት ሃሳብ ሳይሆን ትክክለኛ የኢየሩሳሌም የመፍረስ ምክንያት አድርገው ያዩት ሊሆን ይችላል፤ በአንተ አመለካከት እውነተኛው የመፍረሷ ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
7. ከቁ17-21 ባለው ክፍል ውስጥ ስናነብ ንጉሱ ለተላከለት የክስ ደብዳቤ ምላሽ በላከው ደብዳቤ ውስጥ ስለቀድሞዋ ኢየሩሳሌም በቤተ መዛግብት ውስጥ ተመርምሮ እንደተገኘ የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። ቁ22-24 ላይ ስናነብ እነ ሬሁምና ሲምሳይ የንጉሱ ምላሽ ደብዳቤ በቶሎ እንዲደርሳቸውና የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ ስራ ለማስቆም ቸኩለው እንደነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው?
8. ወደኋላ መለስ ብለን ቁ1-6 ውስጥ ስንመለከት፤ የአይሁድ ጠላቶች የእግዚአብሄርን ቤት ሥራ ለማክሸፍና ለማስቆም የተጠቀሙባቸውን ቢያንስ አራት ታክቲኮች እናነባለን። እነዚህ አራት ታክቲኮች ምን ምንድናቸው? አንተስ በህይወትህ ጠላት በአንድ መንገድ ሲመጣና ሲሸነፍ ታክቲኩን ቀይሮ በሌላ መንገድ የመጣብህን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ጠላታችንን አንድ ጊዜ አሸነፍነው ማለት በሌላ ጊዜ ተመልሶ አይመጣብንም ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርብናል።

# <u>ጥናት አራት ዕዝራ 5፡1-17</u>

የጥናት ዓላማ፡- ቤተ መቅደሱን የሚሰሩት ሰዎች የሥራውን ጥራት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በትጋትና በመፍጥነት ሥራቸውን ያከናውኑ እንደነበረ ሁሉ፤ እኛም የተሰጠንን የወንጌል ሥራ በትጋትና የሥራው ባለቤት መምጫው እንደቀረበ እያሰብን ቶሎ ቶሎ መሥራት እንደሚገባን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን በታላላቅ ድንጋዮች እየገነቡና ቅጥሩንም በወፍራም ምሰሶዎች እየሰሩ ነው፤ ሥራው በትጋት በመከናወንና በእነርሱም አመራር በመፋጠን ላይ ይገኛል።" ዕዝ 5፡8

1. ዕዝራ 5፡1-17 በአንድነት ይነበብ። ቁ1 ላይ "በዚያን ጊዜ" ከሚለው አነጋገር በመነሳት ትንቢተ ሐጌ 1፡2-4 ላይ ነብዩ የሚናገረውን ስንመለከት የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ ቤተ መቅደሱን መሥራትን አስመልክቶ ስለነበረው አመለካከት ምን መረዳት እንችላለን? በዕዝራ 5፡1 ላይ ነብያቱ የመልዕክታቸው ምንጩ እነርሱ እንዳልሆኑ መናገር ብቻ ሳይሆን ምንጩንም በግልጽ ተናግሯል፤ መልዕክታቸው ከየት እንደሆነ ነው የተናገሩት? በክርስትና ህይወትህ ስታይ፤ ከእግዚአብሄር ይልቅ የትንቢታቸው ምንጭ ራሳቸው የሆኑ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ?
2. በቁ3ና በቁ4 ውስጥ በኤፍራጥስ ማዶ ገዢ የነበረው ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው የእግዚአብሄርን ቤት ለመሥራት የተነሱትን አይሁዶች ሁለት ዋና ዋና ጥያቄዎች ሲጠይቁ እናያለን፤ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ነበሩ? እነዚህ ጥያቄውን ያቀረቡት ሰዎች ቀድሞ ሥራው በተጀመረ ወቅት ያስቆሟቸው ሰዎች እንዳልሆኑ ዕዝ 4፡8ትንና ዕዝ 5፡3ትን በማነጻጸር ማወቅ እንችላለን፤ አሁን የጠየቋቸው ሰዎች ይህ መቅደስ ቀድሞ መሰራት ተጀምሮ እንደነበረ እንደሚያውቁ የሚጠቁመን ሃሳብ የቱ ነው?
3. ቁ5 ላይ ጸሐፊው "…ነገሩ ወደ ዳርዮስ ደርሶ የጽሑፍ መልስ እስኪያገኙ ድረስ አልተከለከሉም።" በማለት ይነግረናል። ከዚህ ቀደም ሥራው እንዲቆም ንጉሥ ማዘዙን እያወቁ እነዚህ ተንትናይና ሰተርቡዝናይ የተባሉት ሰዎች ከተባባሪዎቻቸው ጋራ ወዲያው ለማስቆም ስላልቻሉበት ምክንያት ክፍሉ የሚነግረን ነገር ምንድነው?
4. በቁ6-8 ውስጥ ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው ደብዳቤያቸውን ለባቢሎኑ ንጉሥ ለዳርዮስ እንደጻፉለት እናያልን፤ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ እነዚህ የአይሁድ ከሳሾች የእስራኤልን አምላክ ምን በማለት ሲጠሩት ነው የምንመለከተው? እነዚህ የአይሁድ ከሳሾች በእነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ በዚህ የቤተ መቅደስ ሥራ ላይ ተሳታፊ የነበሩት ሰዎች እነማን መሆናቸውን ነው ሲናገሩ የምናየው? ዛሬስ የእግዚአብሄርን ቤት ሥራ ለጥቂቶች የተተወ ነው ወይስ ቅዱሳንን ሁሉ ያሳተፈ ሥራ ነው?
5. በቁ8 ላይ እነ ተንትናይና ሰተርቡዝናይ "ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን በታላላቅ ድንጋዮች እየገነቡና ቅጥሩንም በወፍራም ምሰሶዎች እየሰሩ ነው።" የሚለውን አነጋገር ሲናገሩ ለንጉሥ ዳርዮስ ምን ዓይነት መልዕክት ሊያስተላልፉ የፈለጉ ይመስልሃል?
6. አይሁዳዊያን ቤተ መቅደሱን መስራት ከጀመሩ ጀምሮ እስከ አምስተኛው ምዕራፍ ብቻ ሁለት ጊዜ የክስ ደብዳቤ እንደተጻፈባቸው እንመለከታለን፤ በዕዝ 4፡15 እና በ5፡17 ላይ ስናነብ በሁለቱም ክሶች ውስጥ የተካተተና ሁለቱም ከሳሾች የጠየቁት አንድ ሃሳብ ምን እንደነበረ ተናገር።
7. የእስራኤል ጠላቶች በቁ8 ላይ "ታላቁ አምላክ" በማለት እንደጠሩት ተመልክተናል፤ በቁ9-16 ውስጥ ደግሞ አይሁዳውያኑ ከጠላቶቻቸው ለመጣላቸው ጥያቄ ምላሽ በሰጡበት ወቅት ለእግዚአብሄር የሰጡት ሥም ምን የሚል ነበረ?
8. ቁ8 ላይ ተመልሰን ስናነብ የአይሁድ ጠላቶች ለንጉሱ በጻፉበት ደብዳቤ ላይ የሥራውን ጥራት ብቻ ሳይሆን የሰራተኞቹንም የአሰራር ሁኔታ ጠቅሰው ተናግረዋል። እነዚህ ሰዎች ስለሰራተኞቹ የአሰራር ሁኔታ የጠቀሱት ምን እንደነበረ ተናገር። አንተስ ጌታ እንድትሰራ የሰጠህን ሃላፊነት ምን ያህል በትጋትና ጊዜ እንደሌለው ሰው በፍጥነት ታከናውናለህ? እኛም እንድንሰራው በሃላፊነት የተሰጠንን የጌታ ሥራ ትጋትንና ፍጥነትን በማዋሃድ ማከናወን ይገባናል።

# ጥናት አምስት ዕዝራ 6፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- የእስራኤል ልጆች ደስታቸውን ያገኙት የፋሲካን በዓል በማክበታቸው ሳይሆን ከእግዚአብሄር ስለተሰጣቸው እንደሆነ ሁሉ፤ እኛም ብንሆን ነገሮች ስለተሳኩልና ችግር ከእኛ ስለራቀ ሳይሆን፤ ገላ 5፡22 እንደሚናገረ ደስታ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ስለሆነ መሆኑን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር ደስ እንዲሰኙ ስላደረጋቸው የቂጣን በዓል ሰባት ቀን በደስታ አከበሩ።" ዕዝ 6፡22

1. ዕዝራ 6፡1-22 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ስንመለከት አሕምታ በሚባል ከተማ ውስጥ አንድ ጥቅልል ብራና እንደተገኘ ይነግረናል። የዚህ ብራና መገኘት ወይም አለመገኘት በተለይ በአይሁዳዊያን ታሪክ ውስጥ ሊያስከትለው የሚችለው ነገር ምን ያህል ክብደት ይኖረዋል ብለህ ታምናለህ? አስረዳ። በ6፡1-3 ላይ የተጻፈው ጽሑፍ መገኘቱንና፣ በ1፡1 ላይ የፋርሱ ንጉስ ቂሮስ በጽሑፍ እንዲሰፍር ማዘዙን ስንመለከት ስለ እግዚአብሄር አሰራር ምን መማር እንችላለን?
2. በቁ3-5 ውስጥ ስናይ በጥቅልል ብራና ተጽፎ የተገኘውና የፋርሱ ንጉስ ቂሮስ በጽሁፍ ያሰፈረውን አዋጅ ስናነብ ይዘቱን በሁለት ዋና ዋና ሃሳቦች ከፍለን መረዳት እንችላለን። በአንተ አመለካከት እነዚህ የተተኮረባቸው ሁለቱ ዋና ዋና ሃሳቦች ምንና ምን እንደሆኑ ነው የምትመለከተው?
3. ቁ6ትንና ቁ7ትን ስናነብ ንጉስ ዳርዮስ ለተንተናይ፣ ሰተርቡዝናይና ለተብባሪዎቻቸው የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ በዕዝራ 4፡2-3 ላይ ለእነዘሩባቤል በአካባቢያቸው ከሚገኙት ሰዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ለመለሱላቸው መልስ ማጠናከሪያ ሃሳብ ሆኖ የምታየው በምን መንገድ ነው?
4. የእግዚአብሄርን ቤት ሥራ ለማስተጓጎል ደብዳቤ ለጻፉት ለእነ ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ለተባባሪዎቻቸው ሁሉ በአካባቢያቸው ለሚገኙት ተባባሪዎቻቸው ሁሉ በአይሁድ አካባቢ እንዳይደርሱና ሥራውም በራሳቸው ብቻ እንዲሰራ ከማስጠንቀቁ ሌላ፤ በቁ8-9 ውስጥ ንጉሱ የሰጠውን መመሪያ ስንመለከት ሁለት ነገሮችን መሥራት እንዲችሉ ከመንግሥት ካዝና ወጪ በማድረግ ሳያሰልሱ እንዲተባበሯቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? የእግዚአብሄር ሞገስ ባንተ ላይ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ከጠየቅኸውና ካሰብከብ በላይ የሆነልህን ነገር ታስታውሳለህ ወይ?
5. ቁ10-12 በሚናገረው ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ ንጉሥ ዳርዮስ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ወጥቶ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ እንዲሰራ ከማድረግ ባሻገር የሚሰዋውንም መሥዋዕት ጭምር ለመስጠት ስለተነሳሳባቸው ምክንያቶች የተነገሩት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የንጉሱን አዋጅ የሚጥስና በሚሰራው ቤተ መቅደስ ላይ እጁን በሚያነሳ ሰው ላይ ከራሱ ሌላ እርምጃ እንዲወስድ የተጠራው ሌላ ሃያል ማን ይባላል?
6. የዕዝራን መጽሐፍ ስንመለከት ቤተ መቅደሱን ለመስራት የብዙዎች ርብርብ እንዳስፈለገ እንረዳለን፤ በቁ13 15 ላይ ደግሞ በዚህ ሥራ ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ የነበራቸውን ሰዎች እንመለከታለን፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ብቻ የምታያቸውና ለመቅደሱ ሥራ አስተዋጽዖ አድርገዋል የምትላቸውን ሁሉ በመዘርዘር ተናገር።
7. ቁ22 ላይ "እግዚአብሄር የአሦርን ንጉስ ልብ ለውጦ…" የሚለው አነጋገር በእግዚአብሄር አምላክና በሰው ልጆች መካከል ስላለው ልዩነት ምን ያሳይሃል? አንተስ የሰውን ልብ ለመለወጥ ሞክረህ ያልተሳካልህን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ?
8. ቁ16ትን እና ቁ22ትን ስናነብ ሕዝቡ ሁሉ የፋሲካን በዓል በደስታ እንዳከበሩት ይነግረናል፤ በተለይ "እግዚአብሄር ደስ እንዲሰኙ ስላደረጋቸው…" ከሚለው አነጋገር የሰዎቹ የደስታ ምንጭ ምን እንደሆነ ነው የምናየው? አንተስ የህይወትህ የደስታ ምንጭ እንደሆነ የምታምነው ነገር ምን ይሆን? ለአማኝ ምን ጊዜም ቢሆን የደስታው ምንጭ አድርጎ ሊቀበለው የሚገባው እውነት ቢኖር፤ ደስታችን ከጌታ እንደሚገኝ ማመን ይኖርብናል። ገላ 5፡22ትን ማንበብ ይረዳል።

# ጥናት ስድስት ዕዝራ 7፡1-28

የጥናት ዓላማ፡- ካህኑ ዕዝራ ፈጽሞ ራሱን የሰጠው ለማጥናትና ለማስተማር ብቻ ሳይሆን ቃሉን በተግባት በመኖርም እንደሆነ ሁሉ፤ እኛም ሁላችን ማጥናትና ለሌሎች ማስተማር መልካም ቢሆንም ያጠናነውን ቃል በራሳችን ሕይወት ውስጥ በተግባር መተርጎም አማራጭ የሌለው ነገር እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ዕዝራ የእግዚአብሄርን ሕግ በማጥናትና በማድረግ፣ ለእስራኤልም ሥርዓቱንና ሕጉን በማስተማር ፈጽሞ ሰጥቶ ነበር።" ዕዝራ 7፡10

1. ዕዝራ 7፡1-28 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-5 ላይ ስንመለከት እንደ እኔ አቆጣጠር ከሆነ የዕዝራ የዘር ግንድ እስከ አስራ ስድስት ትውልድ ድረስ ተዘርዝሮ እንመለከታለን። ይንን ያህል ራቅ ብሎ የዕዝራን የዘር ግንድ መዘርዘር ያስፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? መጽሐፉ በዕዝራ ስም ይጠራ እንጂ በቁ6 ላይ እንደምናነበው ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ቤተ መቅደሱ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ እንደሆነ እናያለን። ታዲያ ዕዝራ ገና መምጣቱ ከሆነ ቤተ መቅደሱን የሰራው ማን ነው?
2. በቁ6-7 ላይ ከሰፈረው ሃሳብ ላይ ብቻ በመመርኮዝ ዕዝራ ስለተባለው ሰው ማየት የቻልካቸውን ነገሮች በሙሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር ለወገኖች ተናገር። በንጉስ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የቤተ መቅደሱ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከዕዝራ ሌላ ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሱ የምናያቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
3. ከቁ8 እና ቁ9 ሊሰጡን ከሚችሉት መረጃ በመነሳት፤ ካህኑ ዕዝራ ይኖርበት ከነበረው ከባቢሎን ግዛት በመነሳት ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ የፈጀበት ጊዜ ምን ያህል ነበረ? ቁ9 ላይ "መልካሚቱ የእግዚአብሄር እጅ በእርሱ ላይ ስለነበረች…" ተብሎ የተነገረው ሃሳብ፤ ምኑን አስመልክቶ ይመስልሃል መልካሚቱ የእግዚአብሄር እጅ በዕዝራ ላይ መሆን የጠቀመው? ለነገርህን መሳካት የእግዚአብሄር እጅ በአንተ ላይ መሆን አስፈላጊነቱን ምን ያህል ተረድተሃል?
4. ቁ10-12ትን ስናነብ፤ በተለይም ቁ10 ላይ ዕዝራ ከእግዚአብሄር ቃል ጋራ የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበረ ይነግረናል። ይህ ሰው የእግዚአብሄርን ቃል አስመልክቶ በሕይወቱ ይለማመዳቸው የነበሩት ሶስት ዋነኛ ነገሮች ምን ምን እንደነበሩ ተናገር። በእነኚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት የመጽሐፉ ጸሐፊ ለዕዝራ ሁለት የተለያዩ መጠሪያዎችን ሰጥቶት እናያለን፤ እነኚህ ዕዝራ የተጠራባቸው ሁለት መጠሪያዎች ምንና ምን የሚሉ ናቸው?
5. በቁ13-16 መሰረት ዕዝራ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ወደ እግዚአብሄር ቤት በሚሄድበት ወቅት ይዞ እንዲሄድ ንጉሱ ከሶስት አቅጣጫ ወርቅና ብር ሰብስቦ እንዲወስድ ነግሮታል፤ እነዚህ ሶስቱ ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
6. በቁ17-26 ያለውን ክፍል ስናነብ የንጉሥ አርጤክስስ ንግግር ለዕዝራ ልክ የተፈረመበት ባዶ ቼክ የመስጠት ያህል ነበረ፤ ዕዝራ ይህንን ያህል እንደፈለገ ከንጉስ ካዝና ማውጣት የሚያስችል ሙብት ያሰጠው ነገር ምን ይመስልሃል? ማንነትህና በህርይህ በስምህ ባዶ ቼክ የሚጻፍልህ ዓይነት ነው ወይስ እርሱን ተጠንቀቁት የሚያሰኝ ስም ተሰጥቶሃል?
7. በቁ27 እና በቁ28 ላይ ዕዝራ እግዚአብሄርን ስለ ሁለት ምክንያቶች ሲያመሰግን ይታያል፤ እነዚህ ዕዝራ የሚያመሰግንባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው? ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ሲነሳ ሌሎች ከእርሱ ጋራ ሊሄዱ የሚፈልጋቸውን እስራኤላውያን ማሰባሰብ ስለቻለበት መንገድ ምን ይነግረናል? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከዕዝራ ጋራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ለእነማን ነበሩ?
8. ቁ10 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት ዕዝራ ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበረ ለሚላቸው ከሶስቱ ነገሮች ውስጥ በዚህ ዘመን የምንገው ቅዱሳን ራሳችንን ፈጽመን ለመስጠት የየምንቸገረው ከሶስቱ በትኛው ሃሳብ ነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ቃሉን ከማጥናት፣ ያጠናኸውን ከማድረግ፣ ወይም ያጠናኸውን ለሌላ ከማስተማር የትኛው ይከብድሃል? ቃሉ የምናጠናውና ለሌሎች የምናስተምረው ነገር ብቻ ሳይሆን በህይወታችን የምንተገብረው ነገር እንደሆነ መዘንጋት አይኖርበትም።

# ጥናት ሰባት ዕዝራ 8፡1-36

የጥናት ዓላማ፡- በዚያን ጊዜ መሪ የነበረው ዕዝራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት ግልጽ በሆነ መንገድ በመቁጠር ለሌሎች እንዳስረከበ ሁሉ፤ ዛሬም በቤተ ክርስትያን የሚሰበሰበውን ገንዘብ ከሁለት ባላነሱ ሰዎች ሊያረጋግጥ በሚችሉበትና ግልጽ በሆነ መንገድ በመቆጠርና በመረካከብ ካላስፈላጊ ትችት ቤተ ክርስትያንን መጠበቅ እንደሚቻል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ለኦሪዮ ልጅ ለካህኑ ለሜሪሞት በእጁ አስረከብነው፤ ከእርሱም ጋር የፊንሃስ ልጅ አልዓዛር ሌዋውያኑ የኢያሱ ልጅ ዮዛባትና የቢንዊ ልጅ ኖዓድያ ነበሩ። ሁሉም ነገር ተቆጠረ፣ ተመዘነም፤ የተመዘነውም ሁሉ በዚያኑ ጊዜ ተመዘገበ።" ዕዝራ 8፡34

1. ዕዝራ 8፡1-36 በአንድነት ይነበብ። በንጉሥ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የተሰጣቸውን ወ አገር የመመለስ እድል ተጠቅመው ከዕዝራ ጋራ የተመለሱትን ሰዎች ዝርዝር በቁ1-14 ላይ እናነባለን። ከመመለሳቸው በፊት የተካሄደውን ነገር ከቁ15 ጀምሮ የምናነብ ሲሆን፤ በተለይ ቁ15 ላይ ስታነብ ዕዝራ ሕዝቡን ማሰባሰቡና በዚያም ለሶስት ቀናት ቆይታ ማድረጋቸው ያስገኘው ምን ጥቅም ታያለህ? ዕዝራ እንደገና በቁ18 ላይ "መልካሚቱ የአምላካችን እጅ በእኛ ላይ ስለነበረች" በማለት ይናገራል፤ በዚህ ሥፍራ መልካሚቱ የአምላካቸው እጅ በእነርሱ ላይ መሆኗ የሰራችው መልካም ነገር ምን ነበረ?
2. አስቀድሞ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ከተነሱት እስራኤላውያን በተጨማሪ ለቤተ መቅደሱ አስፈላጊ የነበሩት ሌዋውያን በመጡና ጉዞው ሊጀመር ሲል ዕዝራና ሕዝቡ የወሰዱት የመጀመሪያው እርምጃ ምን እንደነበረ ነው የምናነበው? በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም በቁ21 ላይ ስትመለከት፤ ዕዝራና ሕዝቡ በእግዚአብሄር ፊት ለመጾምና ለመጸለይ የተነሳሱበት ዋነኛ ዓላማ ምን እንደነበረ ተናገር። አንተስ በራስህ ላይ የምታውጀውም ሆነ በቤተ ክርስትያን የሚታወጀው የጾምና የጸሎት ጊዜ እንደ እነ ዕዝራ ግልጽና የማያሻማ መሆኑን ከወገኖች ጋራ ተወያዩበት።
3. በቁ21-23 ላይ ስንመለከት ዕዝራና ከእርሱ ጋራ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለንብረታቸው ደህንነትና ጥበቃን ለማግኘት በተጠቀሙበት መንገድና፤ በነህ 2፡7-9 ላይ ደግሞ ነህምያና ሕዝቡ ደህንነታቸውን አስመልክተው በተጠቀሙበት መንገድ የምታየው ልዩነት ምንድነው? እነዚህ ሁለት የሕዝብ መሪዎችና የእግዚአብሄር አገልጋዮች የተጠቀሙባቸው ሁለቱም መንገዶች በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የነበራቸው እንደሆኑ ከቃሉ ውስጥ የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው እንደሆነ ተናገር።
4. እነ ዕዝራ ጥበቃ እንዲያገኙ ያስፈለጓቸው ዋነኛ ምክንያቶች ምን ምንድናቸው ብለህ ታምናለህ? ይህን ምዕራፍ ስንመለከት ከአህዛብ ወገን የሆነው ንጉሥ አርጤክሥ በኢየሩሳሌም ሊሰራ ላለው የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ብዙ ስጦታ በመስጠት በስራው ሲተባበር እንመለከታለን (ቁ25) ፣ በዕዝ 4፡3 ላይ ደግሞ ሰዎቹ ከአይሁድ ጋራ መቅደሱን ለመስራት ሲጠይቁ ሲከለከሉ ይታያል፤ የንጉሱን ስጦታ ተቀብለው የእነዚህን ሰዎች ትብብር እንቢ ያሉበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?
5. በቁ25-27 ላይ በምታነብበት ጊዜ ለእግዚአብሄር ቤት ስራ በሚሆነው መዋጮ ውስጥ የተሳተፉት ሰዎች እነማን እንደነበሩ በመዘርዘር ተናገር። "እናንተና እነዚህ እቃዎች ለእግዚአብሄር ተቀድሳችኋል" በማለት ነህምያ በቁ28 ላይ የተናገረው አነጋገር ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ አስረዳ።
6. ዕዝ 7፡20-21 ላይ ስናነብ ንጉሥ አርጤክሥ ለካህኑ ለዕዝራ ባዶ ቼክ እንደ መጻፍ ያህል ገንዘብን ብቻ ሳይሆን የፈለገውን ነገር ከመንግሥት ግምጃ ቤት መውሰድ እንዲችል በጣም ሰፊ የሆነና ማዕቀብ የሌለበት ዓይነት ሥልጣን እንደተሰጠው እንመለከታለን፤ በምዕራፍ 8 ውስጥ ስትመለከት ዕዝራ ከንጉሱ የተሰጠው ገደብ ያልነበረው ስልጣን ሕይወቱን እንዳይቦረቡርበት የተጠቀመው ዘዴ ምን ነበረ?
7. ከቁ24 ጀምሮ እስከ ቁ34 ድረስ ያለው ክፍል የሚናገረው ለእግዚአብሄር ቤት ሥራ የተሰበሰበው ወርቅ፣ ብርና ሌሎችም ነገሮች ሁሉ በጥንቃቄ ለመጠበቅ ብዙዎችን ማሳተፍ እንደፈለገ ያሳየናል። ከዕዝራ አደራረግ የእግዚአብሄርን ቤት ንብረት አያያዝ በተመለከተ ልንማር የምንችለው ትልቅ እውነት ምንድነው? የእግዚአብሄር ቤት ገንዘብና ንብረት አንድ ሰው ብቻውን እንደፈለገ ያለምንም ቁጥጥር ወዲያ ወዲህ የሚያደርገው ነገር ሳይሆን በትልቅ ጥንቃቄና በግልጽነት ሊጠበቅ የሚያስፈልገው ነገር ነው።

# <u>ጥናት ስምንት ዕዝራ 9፡1-15</u>

የጥናት ዓላማ፡- "በዕዝራ ዘመን ለእግዚአብሄር ቃል የተንቀጠቀጡትን ሰዎች ወደ ንስሃ እንዳመጣቸው ሁሉ፤ እኛም የእግዚአብሄርን ቃል እንፈራለንና ለቃሉም እንንቀጠቀጣለን የምንል ሁላችን ቃሉ ለሚናገረን ነገር የመታዘዝ ልብ ሊኖረን እንደሚገባ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በደል ከፈጸሙት ምርኮኞች የተነሳም በእስራኤል አምላክ ቃል የተንቀጠቀጡት ሁሉ በዙሪያዬ ተሰበሰቡ።፡" ዕዝ 9፡4

1. ዕዝራ 9፡1-15 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ እንደ መክፈቻ አረፍተ ነገር ሆኖ የቀረበው "እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ" የሚለው አነጋገር ስለ የትኞቹ ነገሮች ነው ጸሐፊው ለመናገር የፈለገው? በቁ1 ላይ እና በቁ2 መጨረሻ ላይ የህዝብ መሪዎችን እንመለከታለን። በቁ1 ላይ በምናያቸው መሪዎችና በቁ2 ላይ በምናያቸው መሪዎች መሃል ግልጽ ሆኖ የምንመለከተው ልዩነት ምንድነው ትላለህ?
2. እግዚአብሄር አምላክ እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ወጥተው ማርና ወተት ወደምታፈሰው አገር ወደ ከነዓን በገቡ ጊዜ በዘዳ 7፡3-4 ውስጥ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ በማየት፣ በዕዝ 9፡1-2 ላይ ተከስቶ የምናየው ሁኔታ የእግዚአብሄርን ማስጠንቀቂያ እውነተኛነት የሚያረጋግጠው እንዴት ነው? እነዚህን ሁለት ቁጥሮች ብቻ ትኩረት በመስጠት ስንመለከት፣ ከአህዛብ ጋራ በመጋባትና በርኩሰታቸው በመሳተፍ እግዚአብሄርን እንደበደሉ የተነገረላቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች ማን ማን እንደነበሩ ተናገር።
3. በቁ3 እና በቁ4 ላይ ስናይ በሓዘን ተመትቶ ራሱን ወደ አምላኩ በጸሎት በመመለስ ከሚገኘው መሪያቸው ከነህምያ ጎን ተሰልፈው የምናገኛቸው ምን ዓይነት ሰዎችን ነው? እነዚህ ሰዎች ማናቸውም ቢሆኑ በጊዜው በሆነው ክፉ ተግባር ላይ የተሳተፉ እንዳልነበሩ ይታወቃል፤ በዚህ እግዚአብሄርን በመበደል ተግባር ውስጥ ያልተሳተፉ ሰዎች ሆነው እያለ ታዲያ ለምንድነው እንደ በደለኛ በእግዚአብሄር ፊት የሚያዝኑት?
4. በዕዝራ 9፡4 ላይ ስለምናያቸው በቃሉ ስለሚንቀጠቀጡት ሰዎች፤ በኢሳይያስ 66፡2 ላይ እግዚአብሄር ሲገባ የምንመለከተው ቃል ኪዳን ምንድነው? በዕዝ 9፡4 ላይ ስለ ዕዝራ የምናነበውን ሃሳብና፣ በነህ 1፡4 ላይ ስለነህምያ የምናነበውን ሃሳብ በማነጻጸር ስናይ እነዚህን ሁለት መሪዎች ምን የሚያመሳስሉባቸው ነገሮች ትመለከታለህ? አንተስ ራስህን ስትመዝነው የእግዚአብሄር ህዝብ ውድቀት ልብህን ሲሰብርህና ሲያስለቅስህ ታገኘዋለህ ወይ?
5. ከቁ5 ጀምሮ እንደምናነበው መጎናጸፊያውንና ካባውን መቅደድ፣ የራሱን ጸጉርና ጢም መንጨት፣ እንዲሁም በነገሩ ደንግጦ መቀመጥ ለዕዝራ ብቻውን በቂ ነገር ሆኖ እንዳላገኘው እንገነዘባለን። ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ በኋላ ዕዝራ ለመውሰድ የወሰነው እርምጃ ምን ነበረ? ቁ6ትን እና ቁ7ትን ስናነብ ዕዝራ ፊቱን ወደ እግዚአብሄር ቀና ማድረግ እጅጉን እንደፈራ እንመለከታለን፤ ይህ ሰው ይህንን ያህል ለመሸማቀቅና የእግዚአብሄርን ፊት ለማየት ያስፈራው ነገር ምን ምንድነው ትላለህ?
6. በቁ7-9 ላይ ያለውን ሃሳብ ስናነብና ዕዝራ ከጸለየው ጸሎት በመነሳት፤ እስራኤላውያን እስለዛሬ ለደረሰባቸውም ነገር ሆነ ዛሬ ሰለሚገኙበት አስከፊ ሁኔታ ተጠያቂ አድርጎ የሚያቀርበው ማንን ነው? ምንም እንኳን ለመጣባቸው ነገር ተጠያቂነቱ የራሳቸው እንደሆነ ቢናገርም እንኳን፤ እነዚህ ቁጥሮች ሌላ የሚያረጋግጥልን ሃሳብ እግዚአብሄር ይህም ሆኖ ቸርነቱን እንዳልነፈጋቸው ነው። የእግዚአብሄርን ቸርነት ያሳያሉ የምትላቸውን ጥቂት ነገሮች ከእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በማውጣት ተናገር።
7. ቁ10-12ትን ስታነብ ዕዝራ እንዲሁ አጠቃላይ የሆነ ንስሃ እየገባ እንዳልሆነና ለተደረገው ሃጥያት ትኩረት ሰጥቶ እንደጸለየ ነው የምናየው፤ በዚህ ወቅት ዕዝራ ያተኮረበት ሃጥያት ምን ነበረ?
8. መለስ ብለን ቁ4ት ላይ ስናነብ "…በእስራኤል አምላክ ቃል የተንቀጠቀጡት ሁሉ በዙሪያዬ ተሰበሰቡ፤" በማለት ዕዝራ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ነው የምትረዳው? አንተስ ለእግዚአብሄር ቃል የምታሳየው አክብሮትና ፍርሃት ምን ያህል ነው?

## ጥናት ዘጠኝ ዕዝራ 10፡1-44

የጥናት ዓላማ፡- ዕዝራ ቃሉን የሚፈልግ፣ የሚያደርግና፣ የሚያስተምር ሰው ብቻ ሳይሆን ለጸሎትም የሚተጋ እንደነበረ ሁሉ፤ እኛም በእግዚአብሄር ቃል እውቀት ላይ ማተኮራችንን ሳንተል፤ ከዚያ በተጨማሪ ለጸሎትም አስፈላጊውን ሥፍራ መስጠት እንደሚገባን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ዕዝራ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ወድቆ በሚጸልይበት፣ በሚናዘዝበትና በሚያለቅስበት ጊዜ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች የሚገኙበት እጅግ ብዙ የእስራኤል ማኅበር በዙሪያው ተሰበሰበ፤ እነርሱም እንደዚሁ አምርረው አለቀሱ።" ዕዝ 10፡1 ዕዝ 7፡10

1. ዕዝራ 10፡1-44 በአንድነት ይነበብ። ከምርኮ ከተመለሱት በቁጥር ትንሽ የማይባሉት ከአህዛብ ጋራ በመጋባት እግዚአብሄርን ስላሳዘኑ የሕዝቡ መሪ የነበረው ዕዝራ በቁ1 ላይ ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? በዚያው ቁጥር ውስጥ ስንመለከት፤ የዚህ የእግዚአብሄር ሰው ለቅሶና በእግዚአብሄር ፊት ራሱን አዋርዶ በጸሎት በአምላኩ ፊት መቅረቡ በሌላው ሕዝብ ላይ ያስከተለው ተጽዕኖ ምን ነበረ? ከዚህ ነገር መማር የምንችለው ምን ነገር አለ ትላለህ?
2. ቁ2-4 ላይ ስንመለከት የይሒኤል ልጅ ሴኬንያ በመባል የተጠራው ሰው ከተናገረው ንግግር ውስጥ ላዘነውና ለቆዘመው ዕዝራ ልቡን ሊደግፍና ሊያነቃቃው የሚችል ሁለት ነገሮችን ጠቅሷል፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህ ሰው መሪውን ለማበረታታትና ከነበረበት ሃዘን ውስጥ ወጥቶ መደረግ ያለበትን ነገር እንዲያደርግ ሲናገር የነበሩበትን ሁኔታ እንዳልነበረ አድርጎ በመካድ እንዳልነበረ ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው?
3. በቁ5-8 ላይ ዕዝራ በሴኬንያ ምክር ተበረታቶ ከነበረበት ሁኔታ እንደተነሳና የተመከረውን ምክር በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊውን ነገር ሲያደርግ ይታያል። በዚህ ክፍል ውስጥ የዕዝራ ሃዘን እንዲያው ለማስመሰል እንዳልነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሕዝቡ እግዚአብሄርን ለበደሉበት ነገር መፍትሄ ለመፈለግ እንዲደረግ የተወሰነው ስብሰባ ጉዳይ ስናይ፤ አዋጁን የቀልድ እንዳልነበረ የሚያስረዳን የትኛው ሃሳብ ነው?
4. በቁ9-11 ውስጥ ስናይ ሕዝቡ ሁሉ የተደረገላቸውን ጥሪ አክብረው እንደተባለው በሶስት ቀን ውስጥ ለስብሰባው እንደመጡ ይታያል። ይህንን ክፍል ስናይ ለህዝቡ ጭንቀት ሆነውበት የነበሩት ሁለት ነገሮች ምንና ምን ነበሩ? ዕዝራ 9፡6 ላይ እዝራ ለእግዚአብሄር በጸለየበት ሰዓት በተናገረው ንግግርና፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በቁ10 ላይ ለሕዝቡ በተናገረው ንግግር መሃል የሚታየው ትልቅ ልዩነት ምንድነው?
5. ዕዝራ በቁ11 ላይ ላቀረበው ሃሳብ ህዝቡ በሙሉ በቁ12 እና በቁ13 ላይ በሃሳቡ ቢስማሙም ጊዜውን አስመልክቶ በሌላ ጊዜ መሆን እንደሚገባው ለሰነዘሩት ሃሳብ ምክንያት አድርገው ያቀረቧቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ዕዝራ ሊያደርግ ከነበረው ነገር የተሻለ ሃሳብ ነው ብለው ያመኑትን የመፍትሄ ሃሳብ በቁ14 ላይ በማቅረብ በብዙዎቹ ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኘ እናነባለን፤ በቤተ ክርስትያንም ሆነ ለተለያዩ ስብሰባዎቻችን ከዚህ ምን መማር እንችላለን?
6. ቁ15 ላይ ከሕዝቡ ሁሉ ተቃውሞ ያቀረቡት ስንት ሰዎች ነበሩ? ከእነዚህ ሰዎች ጋራ ይተባበራል መልካም በሆነው ሃሳብ ላይም ያምጻል ብለህ የማትገምተው ሰው የትኛው ነው?
7. በቁ18-44 ውስጥ ባዕዳንን ሴቶች ያገቡትን ይዘረዝራል። ጸሐፊው ይህንን ዝርዝር ሲያስቀምጥ ሰዎቹን ሁሉ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መድቧቸዋል፤ እንዚህ አምስት ሰዎቹን የመደበባቸው ምድቦች ምን ምን ነበሩ? በእነዚህን በአምስት ምድቦች ውስጥ ያልተካተተ ሰው አለ ማለት ይቻላል ወይ? ከዚህ ሁኔታ ስለ ሃጥያት ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
8. በዕዝራ 7፡10 ላይ ስናነብ "ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግና ያደርግ ዘንድ፥ ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር።" በማለት የዚህን ሰው ለቃሉ ያለውን ትጋት ያሳየናል። በዕዝ 10፡1ላይ ስለዚህ የእግዚአብሄር ሰው የምናየው ሌላኛው ገጽታ ምንድነው? አንተስ ቃሉንና ጸሎትን አብሮ የማስኬድ ልምድ አዳብረሃል ወይ? ምንም ያህል የቃሉ ዕውቀትና የማስተማርም ችሎታ ቢኖረን እንኳን፤ ያለጸሎትና ከእግዚአብሄር ጋራ ግንኙነታችንን ካላጠበቅን ኪሳራ እነደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።